ጌታውን የሚያወሳና የማያወሳ ሰው ምሳሌ እንደ ህያውና እንደ ሞተ ሰው ምሳሌ ነው።

ከአቡሙሳ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ
ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "ጌታውን የሚያወሳና የማያወሳ ሰው ምሳሌ እንደ ህያውና
እንደ ሞተ ሰው ምሳሌ ነው።"» በሙስሊም ዘገባ ደሞ "በውስጡ አላህ የሚወሳበት ቤትና አላህ የማይወሳበት ቤት ምሳሌ እንደ ህያውና እንደሞተ ሰው ምሳሌ ነው።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አላህን በሚያወሳና በማያወሳ ሰው መካከል ያለውን ልዩነት ከጥቅሙና ማንነቱ ከማማሩ አንፃር የነርሱ ምሳሌን በህይወት ባለና በሞተ ሰው ምሳሌ ገለፁ። ጌታውን የሚያወሳ ሰው ምሳሌ ውጫዊ ማንነቱ በህይወት ብርሃን፣ ውስጣዊ ማንነቱ ደግሞ በእውቀት ብርሃን እንደተዋበ ሰው ነው። ጥሩ ነገር ያለውም እዚህ ላይ ነው። አላህን የማያወሳ ሰው ምሳሌ ደግሞ ውጫዊ ማንነቱ ከውበት እንደተራቆተ ውስጣዊ ማንነቱ ደግሞ በጥመት እንደተሞላ ሙት ሰው ነው ምሳሌው። ከርሱም ጥሩ ነገር አይገኝም። ልክ እንደዚሁ ቤትም የሚኖሩበት ሰዎች አላህን የሚያወሱ ከሆኑ በህያውነት ያለበለዚያ ደግሞ ነዋሪዎቹ አላህን ከማውሳት የተራቆቱ ስለሆኑ በሙታን ይመሰላል። ህያውነትና ሙታንነት የሚለው ባህሪ ለቤት ከሆነ የዋለው የሚፈለግበት ቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ነው።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/4177